★ ዴሞክራሲያ ★

ዴሞክራሲያ ቅጽ 36 ቁጥር 2 ጥቅምት-ኅዳር 2003 ዓ.ም

## የመታገል ግዳጅ፤ አይዘሉት አማራጭ

የነብርን ጭራ አይዙ ከያዙ አይለቁ እንደተባለው ሁሉ ትግልን ከጀመሩ ከግቡ ሳያደርሱ መተው የሚገባ አይሆንም፡፡ እሳት እንጨት ካልነፈጉት የሚጠፋ አይደለምና ትግልን ለማስጀመር ለመነሳሳት ምክንያት የሆኑት እስካልጠፉ ወይም እስካልተቀየሩ ድረስ ትግል መቀጠል ያለበት ተልዕኮና ግዳጅ ይሆናል፡፡

ትግል በተለይም አረመኔና ኢሰብዓዊ የሆኑ አገዛዞችንና ገዢዎችን ለማስወገድ የተደረገ ትግል መራራ ነው፡፡ ከባድ መስዋዕትነትን ይጠይቃል፡፡ አንዳንዶች ስብሰባ ጠርተው ንግግር ማድረግና ከገዢዎች ጋር መደራደርና መነታረክን ትግል አስመስለው ሊያቀርቡ ቢጥሩም ወይም ሰላም በሰፈነባቸው ሀገሮች ሊካሄድ እንደሚችለው እምብዛም ጣጣና መከራን እንደማያስከትል አድርገው ቢገምቱትም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የሚካሄድ ሕዝባዊ ትግል የታጋዮችን ደምና ስቃይ ጠያቂ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ያየነው ነው፡፡ በሀገራችን ታሪክ አሰቃቂ ቦታ የያዘው ፀረ ኢሕአፓ ቀይ ሽብር የቅርብ ተመክሮና ምሳሌ ነው፡፡ ጨቋኝና ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዞች ለተቃውሞ ሁሌም መልሳቸው ግድያና አፈና ነውና ትግል መራራ ሆኖ መገኘቱና መካሄዱ ሊወገድ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ትግል ብሎ የሚነሳ ይህንን ተረድቶና መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት/አለባት፡፡ ኢሕአፓ ትግል ብሎ ሲነሳ ይህንን ተገንዝቦ ነበርና ምንም እንኳን እንደሚጠበቀው ሁሉም በጀመረበት ቆራጥነት ፀንቶ ባይቀጥልም እነሆ እስከዛሬ ሲመሠረት ያነሳውን ሰንደቅ እያውለበለበና ቃልኪዳኑንም አክብሮ ቀጥሏል፡፡ የትግልን መራራነት የሚያውቅ ሁሉ ምክንያት በሌለበት መከራና ስቃይ ወልፍ ሆኖበት ትግል ትግል የሚል ጤናማ ሰው እንደሌለ ያውቃል፡፡

ለአያሌ ዓመታት ትግል በፅናት መካሄዱን ከጥፋትና ሐጢያት ሊፈርጁ የሚፈልጉ ክፍሎች ቢኖሩም ትግሉ ለረጅም ዓመታት እየቀጠለ ያለው የተነሱት ጥያቄዎች ባለመመለሳቸውና ጭቆናውም ባለመወገዱ ነው፡፡ ከአፄው ጊዜ ጀምሮ ምላሽ ያላገኘው መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄ ዴሞክራሲን ይመለከታል፡፡ ኢዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች እንዲጠፉ የተደረገው ትግል ገና ድልን አልተቀዳጀም፡፡ የአፄውን ሥርዓት የተካው ወታደራዊ አገዛዝ የባሰ አፋኝና አረመኔ ነበር፡፡ ይህም ሲወገድ ሥልጣን የያዘው ደግሞ ኢዴሞክራሲያዊ ከመሆኑ በላይ ሀገርን እንደ ሀገር ሊያጠፋ የተነሳ ዘረኛ ቡድን ነው፡፡ ዴሞክራሲ ደብዛዛ ገፅታዋም በሀገራችን ባለመታየቱ ለዴሞክራሲ

የተካሄደው ረጅም ትግል ቀጣይ ሆኖ ይገኛል። ከዚህ አጠቃላይ ነጥብ ተነስተን ወደዝርዝሩ ስንገባ ሰማንያ አምስት ከመቶ በላይ ሕዝባችንን በቀጥታ የሚመለከተውና ለሀገሪቷ ዕድገት ዋስትና ሊሆን የሚችለው የመሬት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ አላገኘም። መሬት ለአራሹ ዛሬም ወቅታዊና አንገብጋቢ የትግል መፈክር ሆኖ ይገኛል። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ይባስ ብሎ የሀገርን መሬት ለባዕዳን እየሸጠና አሳልፎም "የናንተ ነው" ብሎ ቆርሶ እየሰጠ መሆኑ ደግሞ የሚታይ ነው። ምን ቢያርሱ ድንበርን አያፋልሱ እውነትም ተረት ሆኗል። ስለዚህም ችግሩ ተባብሷል፤ ይበልጥ ተበለሻሽቷል እንጂ ምላሽ አላገኘም። ዋናና የብዙሁኑ ጥያቄ የሆነው የሕዝብ እኩልነትም እንኳን ምላሽ ሊያገኝ በአስከፊና የሀገርን ሕልውና በሚፈታተን ደረጃ ተይዟል። ኢትዮጵያን መበታተን መርህ ግብሬ ነው ብሎ የተነሳው ወያኔ ሥልጣን ከመጣ በኋላም ለጭቁኖች ቆሜያለሁ በሚል መመፃደቅ የመገንጠል አንቀፅን ሕገ መንግሥት በሚለው በራሱ ሕገ ወያኔው ቢያሰፈርም፤ ብሔረሰብን መሠረት ያደረገ ፌዴራላዊ ሥርዓት አሰፈንኩ ቢልም በመሠረቱ ጭቆናን ቀጥሎ፤ መብትን ነፍጎና ረግጦ፤ የራሱን ጎጠኛ የበላይነት በሕዝብ ላይ ጭኖ፤ ጠላት የሚላቸውን ብሔረሰቦችን እያጠቃ መሆኑ ተረጋግጧል። መድብለ ፓርቲም አለ ተብሎ ሲለፈፍ ከርሞ ሀቁ ይፋ ይውጣ በሚል እነሆ የአንድ ድርጅት የበላይነት ወይም አገዛዝ ይፋ ሆኗል።

ሲሳይ ያለቀበት አንበጣ በድንጋይ ላይ ያርፋል እንደሚባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እየታገለና ደሙን እያፈሰሰ በተደጋጋሚ ግን ድልና ሲሳይን እየተነጠቀ መቀጠል የግድ ሆኖበታል። ሊሆን አይችልም፤ የባሰ ሊመጣ አይችልም እየተባለ ግን የባሰው እየመጣና መብት ረገጣው መረን እየለቀቀና እየተባባሰ፣ የሀገር ሉዓላዊነት ይበልጥ እየተደፈረ ፤ ህግና ፍትሕ እየተቀበሩ ፤ ግፉ ሞልቶ ተርፎ እየፈሰሰ ሲሄድ ማየት ዜጎች ተገደዋል። ታዲያ የመከራው በረዶ ሳይሟሟ፤ የጭቆናው ጨለማ ጠፍቶ በብሩህ የዴሞክራሲ ቀን ሳይተካ እንዴት ትግልን ማቆም ይታሰባል? ዓመት በዓመት ቢተካና ዘመን ቢለዋወጥ የሀገራችን የመከራ እውነታ አልተቀየረም። ሳይታገሉ ጣይ፤ ሳይዋጉ ገዳይ መሆን አሁንም የሚቻል አይደለም። ትግል መቀጠሉ የግድ ነው። ይህ ግዴታ ግን የሁሉም ሊሆን አይጠበቅም። ግዴታውን ሊቀበሉ የሚችሉት ሀገራቸውንና እየተሰቃየ ያለውን ወገናቸውን ከራሳቸው አብልጠው ሊያፈቅሩ የሚችሉት ብቻ ናቸው። ጀግንነትና ድፍረት ደግሞ የዚህ ዓይነቱ ፍቅር ውጤት ናቸው። አለበለዚያ ራስ ወዳድነት ይሰፍንና ይህም አቅፎና አብሮ የሚያመጣውን ፈሪነት ያነግሳል። ፍርሀት ሲሰፍን ደግሞ ዘፈኑ የትግል ሳይሆን የእጅ መስጠትና የፈሪ ለእናቱ መሆኑ አይቀርም። ሆድ አደርነት ይገናል። ሀገርና ሕዝብም ጉዳትን በከባዱ መቀበል ይገደዳሉ። በመሆኑም ፀንቶ መታገልን የሚያክቸለችሉና ከትግል መራቅና ብልህነት ወይም ብልጥነት አድርገው የሚወስዱ የተሳሳቱ ናቸው። ለሀገር ደግሞ ዜጋ የሚታገለው በኮንትራት ለተወሰነ ጊዜና ዓመታት ብቻ ሊሆን ባለመቻሉ፤ "ኢትዮጵያ በቃት ይህን ያህል ዓመት ታገለንላታል" ቋንቋ ትርጉም የለሽ ነው፤ ግዳጅን መተውና ቃል ኪዳንንም ማፍረስ ነው።

የመለስ አገዛዝ ልጡ የተራሰ መቃብሩ የተማሰ ነው። ቁልቁል ወደ ውደቀቱ ጉዞን ጀምሯል ሲባል "ውድቀቱን ትላንት ያርገው" የሚለው ሕዝብ የዚህ አረመኔ 19 ዓመት መቆየት

የሚያቃጥለው በመሆኑ ማመን ሊያዳግተው ይችላል:: በተለይም ለትግል አለሁ የሚለው ክፍል በዝቶ ባለመታየቱና እንደቀድሞው ሳይሆን ዛሬ በርካታ ምሁሮች ሊያውቁ ሲገባቸው ኢትዮጵያዊነትን ትተው ወደ ጠባብነት መውረዳቸው፣ ተመሳስሎ መኖርና በእንንበርከክ መታገል ብልህነት ብለው ከወሳኝ ትግል ሲርቁ፣ ትግልን እንመራለን ያሉት እንኳን ሊመሩ ህልውናቸውን ጠብቀው ለመቆም ሲያቅታቸው ሲያይ ሰፊው ሕዝብ ቀቢፀ ተስፋ ሊያውከው ቢነሳ የሚፈረድበት አይሆንም:: ግን ጨለማው ሲበረታ ኮከቦች ይታያሉ እንደሚባለው ከደይኑ ባሻገር ተስፋ ሰጪ ክስተቶችን ማየትም መቻሉን ማወቅ ያስፈልጋል:: ሆድ አምላኩዎችና ራስ ወዳዶች በመድረኩ ጫጫታ ቢያበዙም ሀቀኛ ሀገር ወዳዶች አሁንም በርክተው አሉ:: ከሀዲና ኅጠኛ ምሁሮች የፈሉትን ያህል የተጀመረውን ትግል እንቀጥላለን፣ ኢትዮጵያን አንክድም፣ ለሆዳችን አድረን ለወያኔ ሰግደን አንዋረድም የሚሉ በርካታ ከምሁሮች አሁንም አሉ:: የትግል መሰረት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አሁንም ያው ኢትዮጵያዊ፣ ያው ለውጥ ፈላጊ፣ ያው አታጋይ ካገኘ ታጋይ ሕዝብ ነው:: ስለዚህም ድልን ነገ እንደምንቀዳጅ እምነታችን ፅኑ ሆኖ በቆራጥነት ትግላችንን መቀጠል ይኖርብናል:: የመለስ አገዛዝ ጎኑ እየሳሳ መጥቷል:: አሌ ብሎ የሚያሰማው ጩኸት የዚህን ሀቅነት ገላጭ ነው:: ጭምብሉን አውልቆ የአንድ ገዢ ፓርቲ ሥርዓትን ማስፈኑ ጥንካሬ ሳይሆን የድካሙ ምልክት ነው:: የራሱ ሙስና፣ ዝቅጠትና ክፍፍል ለውድቀቱ እያዘጋጀው ነው::

ይህ ሐቅ ሆኖ ሳለ ውድቀቱ አለመፋጠኑ የሕዝብ ድርጅታዊ ይዞታ ገና በመሆኑ ነው ማለት ሐቅን መናገር ነው:: ሙት ይዞ ይሞታል ነውና ከሕዝብ ጎራ ተመሳስለው የገቡ የወያኔ ሰርጎገቦች ትግሉን ጎድተውታል:: በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ ባዕዳንም የሕዝብን ትግል አጥቅተዋል:: አስመሳይ ሐዋሪያዎችንም ማመን አዳክሟል:: ከሁሉም በላይ ግን ጠላትና ወዳጅን በቅጡ መለየት ማቃቱና ውዥንብር መስፈኑ ለወያኔ አገዛዝ ጠቅሞታል:: የመለስ አገዛዝ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጠላት ሆኖ ሳለ እንደ ወዳጅ ታይቶ ለድርድርና ለዕርቅ ሲጋበዝ፣ በሁለገብ ትግል ሊወገድ ሲገባው ሰላማዊ ትግል ግን በገቢር ትግል ለምኔ በሆነ አቅዋም ሲያዝ፣...ወዘተ አልፎም ይህን አረመኔ ቡድን ጠላት ብለው በተነሱትና ሕዝብን ሊያስተባብሩ በጣሩት ላይ ሲዘመትና ትግል ሲደናቀፍ 19 ዓመታት አልፈዋል:: ይህን ሁኔታ በመሸፋፈን ሕዝብ ለትግል አልተዘጋጀም፣ ወጣቱ ከፖለቲካ እርቋል፣ ስደት እንጂ ትግል ፈላጊ ትውልድ የለም በሚሉ ሰበቦች ማጠየቂያ ፍለጋውም ስህተት መሆኑን ቢያንስ ወያኔ ሲገባና ከዚያም ወዲህ--ለምሳሌ በ1997--አታጋይ ባገኘበት የተሰዋው ወጣት አሳይቷል:: ብዙሃኑ ወጣት ስደትንም ያገኘና የሚፈልግ አለመሆኑም የሚታወቅ ነው:: ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን ግዳጅ ሊወጡ ያልቻሉት፣ ይመራሉ ሲባሉ የመደናገርና ክፍፍል ነፀብራቅ የሆኑት አለምክንያት አይደለም:: ዕይታቸውና ርዕዮታቸው የጠራ ባለመሆኑ ነው፣ - ከሁሉም በፊት:: ድርጅታዊ ይዘታቸውም ጠንካራ ካለመሆኑም ነው:: የተዛባና ያልተመጣጠነ ግንዛቤና አቅም በመስፈኑም ህብረት ሲሞከር ሳይውል ሳይድር የዘይትና ውሀ ቅልቅል መሆኑ ተደጋግሞ ታይቷል::

ለዓመታት ትግሉን የቀጠሉትንም በግትርነትና በጀመሩበት አቅዋም ሙጭጭ ብሎ በመቆየት የሚከሱት ክፍሎች ደግሞ ያልተገነዘቡት፣ ማንም ድርጅት ቢሆን ላለው ክረምት ድልድይ

ሲሠራ ወይም የዳሸን ተራራን ብርድ በስስ ካኔቴራ ሊጋፈጥ ሲሞክር የሚታይ አይደለም:: በፅናት ትግሉን በመቀጠላቸው አቅዋማቸው አልተቀየረም ብለው (ለምሳሌ ኢሕአፓን) የሚያወግዙት ክፍሎች፣ አንድም የተደረጉትን የመርሀ ግብር መሻሻሎች የማያውቁ ከመሆናቸው ሌላ፣ በዋናው ግን፣ ለምን ፀንታችሁ ታገላችሁ ክስ መሆኑ የሚካድ አይደለም:: መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ ባለማግኘታቸው ጥያቄዎቹ ዛሬም ሲነሱ ይዘታቸው ከቶም ሊቀየር የሚችል አይደለም:: መሬት ለአራሹ፤ መብት ለብዙሃኑ፤ ሉዓላዊነት ለኢትዮጵያ፤ ዴሞክራሲ ለሕዝብ፤ ...ወዘተ ተብሎ ትግሉ ሲቀጥል ይህን ትግል ማንቋሸሽና ማጣጣል አይገባም:: ይህ ደግሞ ግባችንና ዓላማችን ምንድነው፣ ከዚያስ መድረሻውስ መንገድ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል:: ኢትዮጵያንና አልፎም ዓለምን በአዲስ ቅኝ ገዢነት የሚረግጡና የሚበዘብዙ አሉናም እነዚህን ማውገዙ የግድ ይሆናል:: ኢሕአፓ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታና የሕዝብን ፍላጎት በማጤን በ1976 ዓ.ም ሆነ ከዚያም በኋላ በመርሀ-ግብር ደረጃ አስፈላጊ ያላቸውን ለውጦች ያደረገ ሲሆን ከመሪ ርዕዮትም አንፃር ሶሻል ወይም ሕብረተሰባዊ ዴሞክራሲ ይዘቴን ይገልፃል ካለም ዓመታት አልፈዋል:: ይህ ባዶ ቃል ሳይሆን በይዘቱ ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ አለገደብ፤ የብዝበዛ ሥርዓትን መፃረር፤ ሉዓላዊነትን ማስከበር፤ በተጨባጭ ደግሞ አርሶ አደሩን የመሬት ባላቤት ማድረግ፤ ሠርቶ አደሩን መብት ማጎናፀፍ፤ የሀገርን አንድነት በዕኩልነት ማስፈን ዙሪያ ማረጋገጥ የሚሉትን ያቀፈ ነው:: ይህም ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ መብቱ ተከብሮ የሚኖርባትን ኢትዮጵያን ማለቱ እንጂ የአንደኛው አምባገነንነት በሌላው ላይ የሚጫንባት፣ የሚነግሥባት ማለቱ እንዳልሆነም ግልፅ ሊሆን ይገባል::

ስለዚህም ያው ቢሆንም፣ ቢመስልም አዲስ መሆኑ ደግሞ ግልፅ ሊሆን የሚገባው ነው:: የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አልባ በመሆናቸው በፅናትና ሳይሸራረፉ መቅረባቸው ያው ያንኑ መቀጠል ቢመስልም--ቢሆንስ መች ስህተት ሆኖ?--ትግሉ ግን አዲስ ሁኔታና ክስተትን መቋቋም ያለበት ነውና ይዘቱና መፍትሔውም በዚያው መልክ የተለየ ይሆናል:: ሦስት ጨቋኝ ሥርዓቶች መጥተውብናል ቢባልም እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ጠባይና ይዘት አላቸው:: ትኩረታችንን የሚስበው የዛሬው ነውና የወረሳቸውን ችግሮች አባብሶ ቢቀጥልም የራሱን ልዩ ልዩ ችግሮች ቀፍቅፎ የሕዝብና የሀገርን መከራ አበራክቷል:: በዘረኝነት ወይም ጎጠኝነት ወይም በብሄረሰብ ልዩነትና ጭቆና ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ሥርዓት በይፋ አስፍኗል:: ይህ በዚህ ዓይነት ይዘቱና መልኩ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው ቢባል ትክክል ነው:: እንዳለፉት ሥርዓቶች ሁሉ የአርሶ አደሩን የመሬቱ ባለቤትነት ቢፃረርም ከሌሎቹ በተለየ ደረጃ ደግሞ የሀገርን መሬት ለሱዳን አስረክቧል፤ የሀገርን መሬት በርካሽ ለባዕዳን ሰጥቶ አርሶ አደሩን አፈናቅሏል:: የሀገሪቱን የተለያዩ የኤኮኖሚ (የባንክ፣ የኢንዱስትሪ፣ የጅምላና የችርቻሮ፣ ...ወዘተ) ዘርፎችን በአንድ ድርጅት የወያኔ ባለቤትነት ሥር እያስኬደ ይገኛል:: በአንድ ብሔረሰብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ አገዛዝም በመሆኑ ለትግሉ ሌላ ውስብስብ ይዘትን ሰጥቷል:: በምዕራቡ ኃይል የሚደገፍና ከሀገር የቅርብና የሩቅ ጠላቶችም ጋር የወገነ በመሆኑ ለተፃራሪዎቹ ማለትም ለትግሉ በቀላሉ የማይታለፍ ጋሬጣ ዘርግቷል:: በብሔረሰብ ደረጃ ድርጅቶች የበዙ ከመሆኑም ሌላ የሕዝብን የጋራ አንቅስቃሴ የሚያደናቅፉ ሆነው አንድም ከአገዛዙ ጎን ሲሰለፉ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው በጋራው ትግል

የማይታቀፉ ሆነዋል:: ይህንና ሎሎችንም ወያኔያዊ ክስተቶችን በማጤን ዛሬ ዋናው የሀገር ማዳንና የዴሞክራሲ ትግል የሚጠይቀውን ትግል፣ በስልትና በቆራጥነት ማካሄድ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ኢሕአፓ ለሰፊው ህብረተሰብ የሚበጅ ዴሞክራሲን ለማስፈን በሚል ሲታገል ሁኔታዎችን አጢኖና ዛሬም ቢሆን ግን ከትግል ውጪ መፍትሄ አለመኖሩን አምኖና ተቀብሎ ነው::

ሀገርን ለማዳንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ከትግል ውጪ ሌላ መፍትሄ የለም:: በጥገና እርምጃዎች መረባረቡ ህሊናን ቅቤ ለመቀባት ለግለሰቦች ይረዳ እንደሆነ እንጂ የሀገርን መሠረታዊና ከባድ ችግር ከቶም የሚቀርፍ አይሆንም:: በወያኔ ሥርዓት ውስጥ የሚወሰዱ የጥገና እርምጃዎች ውጤታቸው ኢምንት ነው:: ዋናው ግዳጅ ኢትዮጵያን የሚጎዳውን ሥርዓት ማፈራረስና አገዛዙንም ማስወገድ ነው:: ስለዚህም ዋናው ትግል ይህን ግዳጅ ሊወጣ የተነሳ እንጂ በአገዛዙ ሥር ግብረ ሰናይ መሰል እንቅስቃሴ ማድረግ --ያውም ይህም ከተቻለ!-- ሊሆን አይገባም:: ከህገወጡ ሥርዓት ጋር ተቃቅፈውና በሙስና ከበከተው አገዛዝ ጋር በቀጥታም ሆነ በተጨባጭ ተባብረው የጥቅሙ ወይም የፍርፋሪው ተቋዳሽ የሆኑት የሚሰብኩት የቀስ በቀስ ለውጥ ወይም ተቻችሎ መኖር ወይም ማንንም አንደግፍም፣ ማንንም አንቃወምም የሚል ልፈፋ ለሀገር ጎጂ ነው:: ኢትዮጵያ ዛሬ በምትገኝበት ቀውጢ ጊዜ ምላሹ ወያኔንም አንደግፍ ሌላውንም አንደግፍ የሚል ሳይሆን ሀገርን ለማዳን በትግሉ እንሰማራለን የሚል መሆን አለበት:: ሀገር ልትጠፋ ስታጣጥር ሰበቦች ደርድሮ በዝምታ ማየቱና የራስን ኑሮ ማደላደልና መግፋቱ ነገ በታሪክ የሚያስጠይቅ ጥፋት ነው:: ለዚህም ነው ኢሕአፓ አሁንም ቢሆን ለመራራው ትግል አብረን እንነሳ ብሎ ጥሪ የሚያቀርበው - ትግል የግድ በመሆኑ!

ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል የፈሰሰው የብዙ ሺህ ዜጎች ደም የፃፈው ታሪክና ተመክሮ የሕዝብ ቅርስ ነው:: ለቀጣዩ ትግል መሣሪያ ነው:: ለዚህም ነው እንደ ዓይነ ብሌናችን ልንከባከበውና ከታሪክ በራዦችም ጥቃት ልንጠብቀው የሚገባው:: የሰማዕትን ታሪክ መንከባከቡ ለትግል መቀጠላችን አስፈላጊ ነው:: አዲሱን ትውልድ ለማስተማርና ለሀገር መሞት ሕይወትና ዳግም ትንሳዔ መሆኑን ለማስረዳትም ይጠቅማል:: ከዛሬው ትውልድና ሕዝብ ፊት ተደቅኖ ያለው አቢይ ጉዳይ የሕዝብን ያልተከበሩ ሠረታዊ ጥያቄዎችን ማስከበርን ይመለከታል:: ይህን እውን ለማድረግ ህልውናዋ በወያኔ የተጠቃውን ሀገራችንን ለማዳን መረባረብም የማይታለፍ ግዳጅ ይሆናል:: ሀገርና ለዴሞክራሲ መታገል የማይነጣጠሉ ናቸው:: ድሉን በተደጋጋሚ የተቀማ ሕዝብ የዴሞክራሲን ጉዳይ ለሌላ ጊዜ ተወው የሚልን ማዘናጊያ ሊያዳምጥ አይገባውም:: በአንፃሩ ደግሞ መብታቸውን አስከብረው እንዳሉ ሕዝቦች በመለስተኛ ጉዳዮች ሁሉ ሊነታረክና ጊዜ ሊያጠፋ የሚፈቅድለት ሁኔታ የለም:: ኢሕአፓ ይህን ሁሉ ተረድቶ ትግሉን ቀጥሏል፤ ትግሉም ይቀጥል ይላል::

ጥሪው የኢትዮጵያ እንጂ የድርጅት አይደለም:: ጆሮ ያለው ይስማ!!